ሚያዚያ (April) 1, 2011

ውድ የዲሲፒኤስ ቤተሰቦች፣

ለ 2011-2012 ዲሲፒኤስ የትምህርት ዓመት የምዝገባ ሂደት መጀመሪያው ጊዜው አሁን ነው። እንዲሻሻሉ የጠየቋቸውን እና ልጆች ዎም ሊያገኙ የሚገባቸውን ሁኔታዎች ለማሻሻል መሥራት የሚገባንን ተግባር እንቀጥላለን። ዲሲፒኤስ፣ በሁሉም ቀጠናዎች ለሚገኙ ተማሪ ዎች፣ እንደቀስቃሻና አነሣሽ ያሉ የሥነ ጥበብ ቅንጅቶችን የመሳሰሉ፣ የዓለም ቋንቋዎች እና ባህል፣ ሣይንስ፣ ቴክኖሎጂ፣ ምህንድ ስናና ሂሳብ (STEM) በርካታ አማራጭ ፕሮግራሞችን ያቀርባል። የፈተና ውጤቶች ከፍ ብለዋል፣ እንዲሁም የለጋ የልጅነት ትምህርት፣ በከፍተኛ ሁኔታ እየጨመረ ከሚጓዘው የመቀመጫዎች ፍላጎቶች ችግር ጋር፣ ክፍሎች እየጨመሩ መሄዳቸው ይቀጥላል። ከ 1969 ጀምሮ ለመጀመሪያ ጊዜ፣ ዲሲፒኤስ፣ በአጠቃላይ ወደ 1,000 በሚጠጉ ተማሪዎች ያህል የተመዘጋቢ እድገት ጭማሪ አሳይቷል።

እነዚህ እና ሌሎችም ለውጦች ዲሲፒኤስን የተሻለ የትምህርት ሥርዓት እያደረጉት ለመሆኑ ሙሉ እምነት አለኝ። ቀና በሆኑ ገንቢ አስተ ያየቶች እና ከአለፉት ሁለት የትምህርት ዓመት፣ የጎላ የትምህርት ቤቶች ፍላጎቶች መጨመሩን በመገንዘብ፣ በዚህ ዓመት የምዝገባ ሂደ ቱን ቀደም ብለን ጀምረናል።

**ቀደም ብሎ መመዝገቡ ጥቅሙ ምንድን ነው?**
ቀደም ብሎ መመዝገብ፣ ለእያንዳንዱ ትምህርት ቤት የሚፈልገውን የተማሪዎች ብዛት በቅድሚያ በማመልከት፤ ተመጣጣኝ የሆነ መም ህራን እና ሠራተኞችን ለመቅጠር ከማስቻሉም በላይ ተገቢ የመማሪያ እና ማስተማሪያ መጻሕፍት ብዛትን እና የትምህርት መሣሪያዎችን ለማዘዝ ይረዳል። በመጨረሻም የቀደም ብሎ ምዝገባ፣ የ 2011-2012 የትምህርት ዓመት የትምህርት ቤት መከፈት የሰከነ መልክ እንዲኖረው ያስችላል። በዚህ በአብዛኛው ችግሩ እየተባባሰ እንዳይሄድ ለማድረግ ባደረግነው ከፍተኛ ጥረት ሂደት ምክንያት፣ በዲሲፒኤስ ትምህርት ቤቶች ምዝገባ እያደገ በመጓዝ ላይ ይገኛል።

***ከዚህ ጋር ተያይዘው የቀረቡትን ቅጾች ይሙሉ እና በተቻለ መጠን እባክዎን ወዲያውኑ ወስደው ለልጅዎ ትምህርት ቤት ያስረክቡ። የሕዝብ ባልሆኑ ትምህርት ቤቶች ለመማር ከዲሲፒኤስ ገንዘብ የሚያገኙ የልዩ ትምህርት ተማሪዎች ወላጆች፣ ቅጾቻቸውን ለ Office of Special Education (1200 First St. NE, 9th floor) (ልዩ ትምህርት ጽሕፈት ቤት) ወይም የሕዝብ ወደ አልሆኑ ትምህርት ቤቶቻቸው ወስደው ሊያስረክቡ ይችላሉ።*** ማንኛውም ዐይነት ጥያቄዎች ካሉዎት፣ እባክዎን በቀጥታ የልጅዎን ትምህርት ቤት ወይም የዲሲፒኤስ ማዕከላዊ ጽሕፈት ቤትን በ 202-442-5885 ስልክ ደውለው ለማነጋገር አያመንቱ።

ወላጆች ማመልከቻዎቹን በቀላሉ መሙላት እንዲችሉ ለማድረግ በሚደረግ ጥረት፣ ወረቀት አልባ የሆነ ምዝገባ ለማስተዋወቅ የሚያስ ችል ተግባር እያከናወንን፣ ከጥራዙ ውስጥ በርካታ ገጾችን በማውጣት፣ የቅጹ አሞላል ለወላጆች ቀላል ሆኖ እንዲገኝ ጥረት ማድ ረጋች ንን እንቀጥላለን። ቅጹን ሞልቶ በማጠናቀቅ አኳያ የበለጠ እርዳታ እንዲደረግልዎ፣ ዲሲፒኤስ እርስዎን የሚመለከቱ አብዛኛዎቹን መሠ ረታዊ መረጃዎች የሚይዙ ቅጾችን ለቤተሰብዎ ሰጥቷል።

ለ 2011 – 2012 የትምህርት ዓመት ልጅዎን አንዱ ወደ ሆነው ወደ አንዱ ትምህርትቤቶቻችን ለመላክ ምርጫዎ በማድረግዎ እናመ ሰግንዎታለን። የልጅዎን የመማር ፍላጎት ለማርካት እና ተግባራዊ የሥራ እንቅስቃሴ ለሚጠይቀው ለመጭው የትምህርት ዓመት ከእርስዎ ጋር አብሮ ለመሥራት በጉጉት እጠብቃለሁ።

ከልባዊ ሠላምታ ጋር፣

Kaya Henderson
ተጠባባቂ ቻንስለር